**Auckland Regional Public Health Service**

**Rātonga Hauora ā Iwi o Tamaki Makaurau**

Working with the people of Auckland, Counties Manukau and Waitemata

**Auckland Regional Public Health Service**

**Rātonga Hauora ā Iwi o Tamaki Makaurau**

Working with the people of Auckland, Counties Manukau and Waitemata

# ሐኪምህ ወደ ልዩ ሐኪም (ስፐሻሊስት) ወደ ሆስፒታል ወይም ክሊኒክ ሲያስተላልፍህ

**Doctor Referral— Amharic**

**July 2011**

ሐኪምህ ወደ ልዩ ሐኪም (ስፐሻሊስት)ወደ ሆስፒታል ወይም ክሊኒክ አስተላልፎሃል። አገልግሎቱ ነጻ ነው ምንም የምትከፍለው ገንዘብ የለም።

ከሆስፒታሉ ወይም ክሊኒኩ የቀጠሮ ግዜና ሰዓት የሚነግር ደብዳቤ ይላክልሃል። አብዛኛው ግዜ ቀጠሮው ለማግኘት ቢያንስ ሶስት ወር ይወስዳል።

ደብዳቤው ሲደርስህ በደንብ አንብበው ወይም ሌላ ሰው እንዲያነብልህ ጠይቅ። በቀጠሮህ እንደምትገኝ ለማረጋገጥ ማዘዣውን በደንብ መከተል አለብህ።

አስፈላጊ ከሆነ ከሆስፒታሉ ወይም ክሊኒክ አስተርጓሚ መጠየቅ ትችላለህ። ከፈለግክ ወንድ ወይም ሴት አስተርጓሚ በምትናገረው ቋንቋ የሚናገር መጠየቅ ትችላለህ።

የቀጠሮው ጊዜ መለወጥ ወይም ማስቀረት ከፈለግክ ወደ ሆስፒታሉ ወይም ክሊኒኩ መደወል አለብህ።

በቀጠሮ ጊዜህ ካልተገኘህ ሌላ ቀጠሮ ለመውሰድ ረጅም ጊዜ ሊወስድልህ ይችላል ወይም ከቆይታው ዝርዝር ልትፋቅ ትችላለህ።

ሆስፒታሉ የሕክምና ሰነድ ወደ ሐኪምህ ይልካል። የቤት ሐኪምህ ከአንድ በላይ ከሆነ፤ ሰነዱ ወደ ሆስፒታል ወይም ክሊኒክ ያስተላለፍህ ሐኪም ይላካል።

ወደ ሆስፒታል ወይም ክሊኒክ ቀጠሮ ለመሄድ እቀዳ ማዘጋጀት ያስፈልጋል።

ከቀጠሮህ ሰዓት በፊት ወደ ሆስፒታል ወይም ክሊኒክ የሚያደርስህ መጓጓዣ ማግኘት አለብህ። የመጀመሪያህ ጊዜ ከሆነ ከሳላሳ ደቂቃ በፊት ወደ ሆስፒታሉ ወይም ክሊኒኩ መድረስ ሞክር። በሰዓትህ መገኘት በጣም አስፈላጊ ነው አለበለዚያ ተራህ ሊያመልጥህ ይችላል።

ልጆች ካሉህ ቤተሰብ ወይም ጓደኛ ቤትህ ውስጥ ወይም ካንተ ጋር ሆስፒታሉ ድረስ መጥተው እንዲጠብቁልህ ብትጠይቅ ይረዳሃል። ይሄን ማዘጋጀት የራስህ ኀላፊነት ነው።